# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

**አጭር አጠቃላይ ስብሰባ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ሴል ግሩፕን በተመለከተ አጭር አጠቃላይ ስብሰባ ስለሚኖረን ሁላችንም ከቃል በኋላ ወደ ኋላ እንድንቀር ሽማግሌዎች ያሳስባሉ። ጌታ ይባርካችሁ!

**የእህቶች ፕሮግራም**

የቤተ ክርስቲናችን የእህቶች አገልግሎት በNovember 9 ከ 3 p.m. እስከ 5 p.m. የቃል፣ የጸሎትና የህብረት ጊዜ ፕሮግራም ለህቶች ሁሉ መዘጋጀቱን በደስታ ይገልጻል። ቦታው በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ይሆናል። እህቶች ሁሉ ተጋብዛችኋል። ወንድሞች እህቶች እንዲካፈሉ እንድታበረታቱ አገልግሎቱ ያሳስባል።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ።

**እርስ በርስ እንተያይ**

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

“ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።” (ሐዋ. 16፡ 30-31)



⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2፡10

## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




“መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል።”
(ራዕይ 22:17)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**November 3, 2019** | **ጥቅምት 23፣ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

**ጸሎት** ........................... ወንድም ጌቱ ጳውሎስ

**አምልኮ**.......................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

**ፕሮግራም መሪ** ............ ወንድም ሲሳይ መሸሻ

**ቃል** ................................ ወንድም ፈይሳ ወሰኑ

**የጌታ እራት**...................... ወንድም ሲሳይ መሸሻ

**ማጠቃለያ** ...................... ወንድም ሲሳይ መሸሻ

## የሳምንቱ ጥቅስ

"ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፦ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።"
(1ቆሮ. 11:24-25)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ለመታሰቢያዬ አድርጉት

የእግዚአብሔር ቃል የጌታን እራት ስንወሰድ ለጌታ መታሰቢያ እንድናደርገው ያስተምረናል። ለመሆኑ የጌታን እራት ስንወስድ የምናስበው ምንድን ነው? አንደኛ በጌታ የተደረገልንን እናስባለን። ይህም ማለት ስለ እኛ ደህንነት የተቆረሰልንን የጌታን ስጋ እና የፈሰሰልንን የጌታን ደም እናስባለን። እንጀራውን ቆርሰን ስንወስድ የስጋው መቆረስ ምሳሌ ነው። ጽዋውንም ቀድተን ስንጠጣ የደሙ መፍሰስ ምሳሌ ነው። ይህ ደግሞ ለተካፈልነው ሕይወት መሰረት ነው። ጌታ ኢየሱስ በቃሉ እንዳለ የጌታን ስጋ የበላ ደሙንም ደግሞ የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። ከርሱ ጋራም ህይወትንና ትንሳኤን ይካፈላል (ዮሐ. 6:54,56)። እኛ ሕይወት ያገኘነው በጌታ ሞት ነው። ሞቱ የኛ ሞት ነው። በደሙም ከሃጢያታችን ታጠብን። በጌታ ሞት ከአብ ጋራ ታረቅን። በስጋው መቆረስ ለኛ ተዘግቶ የነበረው መጋረጃ ተቀዶ ወደ አብ የምንቀርብበት አዲስና ህያው መንገድ ተከፈተልን። ስለዚህም የጌታን እራት ስንወስድ አንዱ የምናስበው የጌታን ሞት ነው።

የጌታን እራት ስንወስድ የምናስበው ሁለተኛው ነገር ይህንን ስርዓት በእምነት ስናደርግ አሁን በሕይወታችን የሚሰራውን ነው። ቃሉ እንደምያስተምረን "ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና" ይለናል(1ቆሮ. 11:26)። እንጊዲህ ከእንጀራውና ከጽዋው ስንካፈል የጌታን ምት ለመናገር አቅም እናገኛለን። ይህም ማለት ሞቱን፣ በሞቱም ያገኘነውን ሕይወት እንዲሁም በሞቱ የተገለጸው ፍቅር በህይወታችን አዲስ ሆኖ መንፈሳዊ ግለትን ያመጣልናል። ስለዚህም ጌታ ወዶኝ ሞቶልኛል እንላለን፤ ለሌሎችም ይንን አስደናቂ እውነት እንመሰክራለን። እዚህ ላይ በክፍሉ እንደምናነበው የጌታን እራታ ሳይገባቸው (ሳይረዱት ወይንም ህይወታቸውን ሳይመረምሩ) የሚወስዱ ሁሉ ሊደክሙ፣ ሊታመሙ ሊያንቀላፉም ይችላሉ (ቁ. 30)። ይህ እንግዲህ የጌታ እራት በአማኙ ውስጥ የሚሰራው ስራ እንዳለ ያሳየናል። ሳይገባቸው የወሰዱ ከደከሙ፤ ተገብቷቸው የሚወስዱ ደግሞ ይበረታሉ። ሳይገባቸው የሚወስዱ ከታመሙ፤ ተገብቷቸው የሚወስዱ ደግሞ ይፈወሳሉ። ሳይገባቸው የሚወስዱ ካንቀላፉ፤ ተገብቷቸው የሚወስዱ ደግሞ የበዛ ሕይወት ይሆንላቸዋል።

የጌታ እራት በሶስተኛ ደረጃ የጌታን ዳግም ምጽአት ያሳስበናል። በቃሉ እንዳየነው እንጀራውን በበላን ጊዜና ጽዋውን በጠጣን ጊዜ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን እንናገራለን። በዚህ ቃል ውስጥ የጌታ መምጣት ተስፋ ተሰጥቶናል። ጌታችን ወደ መስቀል ከመሄዱ በፊት "ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ" ብሎናል (ዮሐ. 14:1-3)። ጌታ ዳግመኛ ይመጣል። መጥቶም ወደ ራሱ ይወስደናል። ቃሉ የታመነና እውነት ነው። እንዲሁም ደግሞ ጌታ ይህንን ስርአት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሲያደርግ እንዲህ አለ፡ "ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም" (ማቴ. 26:29)። እንግዲህ የጌታን እራት ስንወስድ ሌላው የምናስበው ከጌታ ጋር በእግዚአብሔር መንግስት እራት እንደምንካፈል ነው። ይህ የተባረከ ተስፋችን ነው። ጌታ ይመጣል። አዎን ማራናታ!